# ወደ ABA እንኳን ደህና መጡ

ብርሀ ኣፍሪካውያን አካደሚ (*Accademy of Bright Africans*, ABA) ፕሮጀክት ተጸንሶ የበቀለው ማርያም ሳምቤ በአስራዎቹ እድሜ በነበረችበት ግዜ ለማቋቋም ባለመቸው መሰረት ነው። እ.ኤ.አ በ2006 ለፕሮጀክቱ ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ ዋና ዋና ሃሳቦችን አመነጨች። በመቀጠል ትኩረትዋን በአፍሪካ ቀጣይነት ያለውን እድገት ሊያመጣ የሚችል ሁለገብ ትምህርት ስለመጀመር ሆነ። ይህንንም ፕሮጀክት በትውልድ አገርዋ ኢትዮጵያ ለመጀመር አቀደች። የህዝብን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት ለማረጋገጥ ህብረተሰቡን ገንቢ እንቅስቃሴዎች ሊያደርግ የሚችልበት አካባቢ ለማስገባት አስባ ተነሳች። ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ልጆችን፡ አስተማሪዎችን፡ ሌሎች የት/ቤት ባልደረቦችና ወላጆችን አቅፎ የያዘና ሁሉንም ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችልን የትምህርት ቀመር ከማስጀመር የተሻለ ነገር አለን?

በ ABA የሚሰጠው ሁለ ገብ ትምህርት የተመሰረተው 'እያንዳንዱ ሰው ማንነቱንና የህይወትን ትርጉም እና አላማን ከማህበረሰብ ከአለም እና ከበጎ ተግባሮች ማለትም አዛኝነትንና ፍቅር ጋር ግንኙነት በመፍጠር ነው ከሚል የትምህርት ፍልስፍና ነው' (Miller 1997)። በሌላ አገላለጽ ተማሪዎች በህይወት ለመቆየት ከተፈጥሮ ከማህበረሰቡ እና ከበጎ ተግባሮች ጋር መገናኘት አለባቸው። መከባበር ፍቅር አዛኝነትና ሰላም ከቀለም ትምህርት ውጤታማነት ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው መሄድ አለባቸው። ሁለ ገብ ትምህርት ይሄን ተገባራዊ ለማድረግ ያስችላል። ጆን-ጃክ ሩሶ (Jean-Jacques Rousseau) ስለ ሰው ሁለገብ ትምህርት እድገት ያጠና ፈላስፋና አስተማሪ ነው። ልጆች መማር ያለባቸው አካባቢያቸውን ቤተሰባቸውንና እራሳቸውን በሚገነዘቡበት መልኩ መሆን አለበት ብሎ ያምናል። ልጆች ከአካባቢያቸው መማር እንደመቻላቸው መጠን ይህን ከግምት ውስጥ ማስገባት ለእድገታቸው ቁልፍ ነው (Miller 2007)።

በሁለ ገብ ትምህርት እንቅስቃሴ መሪ ከሚባሉት አንዱ ሮን ሚለር (Ron Miller 1992) እንደሚለው ሁለ ገብ ትምህርት የማይቀያየር አንድ ወጥ ቴክኒክ አይደለም። ይልቅ እንደ ተማሪዎቹ ባህል እና ፍላጎት መቀያየር ያለበት ቀመር ነው። በመሆኑም ABA ለሚመጡ ልጆች ባህል እና ፍላጎታቸውን በተደዩ የሚያይ ሁለ ገብ ትምህርት ይቀርጻል።

Translated from the English by Hanna Mebrahtu
Edited by Mariam Sambe

Copyright © 2014 Academy of Bright Africans (ABA)